# የኢትዮጵያ መንግስት ልማታዊ መንግስት ነውን?

በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ልማታዊ መንግስት፣ ልማታዊ አርሶ አደር፣ልማታዊ ባለሃብት፣ ልማታዊ ምሁር ወዘተ የሚሉ ቃላት መስማት የተለመደ ብቻ ሳይሆን የቀን ተቀን መነጋገርያም ሆኗል:: የኛ ብቻ መገለጫ በሚያስመስል መልኩ ተለጥፈውብን ከነበሩ የጦርነት፣ረሃብ፣ ድህነትና ኃላ ቀርነት አጀንዳዎች እየተላቀቅን ዜና እና ወሬያችን ስለልማት መሆኑ ተመስገን የሚያስብል ነው::

ስለ ልማታዊ መንግስት ሲወራ የልማታዊ መንግስት መገለጫዎች እና ልዩ ባህርያት ምንድን ናቸው? ልማታዊ መንግስት የሚባለውስ ማን ነው? ተብሎ መጠየቁ አይቀርም:: በመሆኑም በዚህች አጭር ጽሑፌ የልማታውያን መንግስታት ባህርያትና መገለጫዎችን በአጭሩ በመዳሰስ ከነዚህ በህርያት እና መገለጫዎች አኳያ የኢትዮጵያ መንግስት ልማታዊ መንግስት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለማየት እንዲሁም የልማታውያን መንግስታት በዚህ ረገድ ካጋጠሙዋቸው እና ከሚያጋጥሙዋቸው ተግዳሮቶች አንጻር አገራችን ሊያጋጥምዋት ስለሚችሉ መሰናክሎች እና መወሰድ ስለሚገባቸው የመፍትሔ አቅጣጫዎች አጠር አድርጌ ለመጠቆም እሞክራለሁ::

***የልማታዊ መንግስት እንደ ኢኮኖሚ ሞዴል ሲገለጽ « በሊበራል የኢኮኖሚ ሞዴል እና በእዝ የኢኮኖሚ ሞዴል መካከል የሚቀመጥ፣ ካፒታሊስትም ሶሻሊስትም ያልሆነ፣ ነገር ግን የሁለቱም ሞዴሎች በጎ ገጽታዎች (የግሉ ሴክተር በጎ ገጽታ እና የመንግስት አዎንታዊ ሚና) በማጣመር የተቀመረ የኢኮኖሚ ሞዴል ነው ይላሉ::» (Woo-Cumings 1999)***

***በሌላ መልኩ ልማታዊ መንግስት ማለት የአንድን አገር የሚኮኖሚ አቅጣጫና ፍጥነት (ሂደት) ለመደገፍና ለመቆጣጠር በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ የሚገባ መንግስት ማለት ነው ይላሉ::***

ወጣም ወረደ ግን አብዛኛዎቹ ተመራማሪዎች በአንድ ሃሳብ ላይ ይስማማሉ:: በታዳጊ አገሮች የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት የሚያስችሉ ስልቶች የሚቀይስ፣ ሁኔታዎች የሚያመቻች እንዲሁም የሚቆጣጠር አካል መኖር እንዳለበት:: በማያያዝ *የልማታዊ መንግስትነት አስተሳሰብ መርህ የሚከተል መንግስት የኒዮ-ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ወደ ጎን በመተው የጣልቃ ገብነት (Interventionism) አስተሳሰብ የተቀበለ መንግስት መሆኑንም ያስቀምጣሉ::*

*የልማታዊ መንግስት ውልደትና እድገት በአውሮፓና ኤዢያ ክፍላተ አሕጉራት እንደሆነ በርካታ የምጣኔ ሃብት ተመራማሪዎች በምርምሮቻቸው አስፍረዋል:: ለዚህም እንደማጣቀሻ እንግሊዝ በሄነሪ 7ኛ (እ.ኤ.አ ከ 1485) ጀምሮ መንግስት በገበያ ውስጥ በቀጥታ እጁን በማስገባት የአገሪቱን አምራቾች ለመደገፍ፣ ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ምክንያት ከውድድር ውጪ እንዳይሆኑና ገበያ እንዳያጡ ለማድረግ ለ 235 ዓመታት የዘለቀ (Protectionism policy)*

በስራ ላይ በማዋል የአገር ውስጥ አምራቾችና ኢንዱስትሪዎች በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እስከሚሆኑ ድረስ በመንግስት እጅ ጠንካራ ቁጥጥርና ድጋፍ ሲደረግላቸው እንደነበር ያብራራሉ::

በፈረንሳይ እንደዚሁ ከ ሉዊ 14ኛ ዘመነ መንግስት ጀምሮ (እ.ኤ.አ 1683) ለ 32 ዓመታት የዘለቀ የመንግስት ቀጥተኛ ቁጥጥርና ድጋፍ ለኢንዱስትሪዎች አድርገዋል:: በተመሳሳይ መልኩ ጀርመንም እ.ኤ.አ ከ1713- 1786 ድረስ ለ 73 ዓመታት የቆየ የኢንዱስትሪ ልማት ማበረታቻ ለማድረግ መንግስት በቀጥታ ጣልቃ በመግባት ይቆጣጠር እንደነበር ይገልጻሉ:: በአውሮፓ በነዚህ ጊዜያት የተጀመሩ የመንግስት በኢኮኖሚ ላይ ጣልቃ ገብነት አሁን በምድረ አውሮፓ በስፋት ለሚታየው « Welfare state political economy » መነሻዎች ናቸውም ይላሉ::

አሜሪካም ብትሆን ቢያንስ እ.ኤ.አ ከ1789-1816 የአሜሪካ ኢንዱስትሪዎች ከውጭ ተወዳዳሪዎች በመጠበቅ አስተማማኝ የውድድር ደረጃ ላይ እስከሚደርሱ ድረስ በተለይ በጥጥ ኢንዱስትሪ ላይ ያነጣጠረ ቀጥተኛ የመንግስት ድጋፍና ቁጥጥር ይደረግ እንደነበር የምርምር ጽሑፎች ያስረግጣሉ::

የኤዢያዎቹ ጃፓን፣ ደቡብ ኮርያ፣ ታይዋን እና ሲንጋፖርም ዓለም ያስደነቀ የኢኮኖሚ እድገት ሊገነቡ የቻሉት የልማታዊ መንግስት መርህ በመከተል ነው:: በተለይ በጃፓን ከሜጂ (Meiji) ዘመነ መንግስት ጀምሮ የነበረው የልማታዊ መንግስት አስተሳሰቦች እና አሰራሮች ጃፓን አሁን ለደረሰችበት የኢኮኖሚ ደረጃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደነበረው ይነገራል::

እንደ አውሮፓውያኑ እና ኤዢያዎቹ በፍጥነት መጓዝ ባይችሉም የተሻለ ኢኮኖሚ እያስመዘገቡ የሚገኙት የደቡብ አሜሪካዎቹ ብራዚልና ሜክሲኮም ከስኬታቸው በስተጀርባ ይሄው የልማታዊ መንግስት ፖሊሲዎች ተከትለው ይሰሩ ስለነበሩ ነው::

ስለ ልማታዊ መንግስት አመጣጥና ምንነት በአጭሩ ይህንን ካልን የልማታዊ መንግስት መለያ ባህርያት ማየቱ አንድን መንግስት ልማታዊ ነው ወይም አይደለም ለማለት መንደርደርያ ስለሚሆን እንደሚከተለው ተቀምጧል::

## የልማታዊ መንግስት መለያ ባህርያት ምንድን ናቸው?

### 1. የመንግስት ጣልቃ ገብነት (Government Intervention)

በልማታዊ መንግስት ምንነት ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ልማታዊ መንግስት ሙሉ በሙሉ የእዝ ኢኮኖሚ የሚከተል ባይሆንም ከኒዮ-ሊበራሊዝም በእጅጉ የራቀ በመሆኑ ለልማቱ መፋጠን የመንግስት እጅ በኢኮኖሚው ውስጥ ጠንካራ እንደሚሆን ለመረዳት ይቻላል:: በመሆኑም በልማታዊ መንግስታት በተለያየ መልኩ የሚደረግ የመንግስት ጣልቃ ገብነት

አይቀሬ ይሆናል ማለት ነው:: እዚህ ላይ ግልጽ መሆን የሚገባው ቁም ነገር መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ የሚገባው በደርግ ጊዜ እንደነበረው ከቀበሌ ሱቅ ጀምሮ እስከ ትላልቅ ኮርፖሬሽኖች ማስተዳደርን ሳይሆን በልማታዊ መንግስት የሚኖር ጣልቃ ገብነት መንግስትና አገሪቱ ሊደርሱበት ወደሚያስቡት የእድገትና የልማት ደረጃ ለመድረስ የሚያስችሉ በተለይ ኢንቨስትመንቶችን አቅጣጫ የማስያዝ፤ የበለጠ ለውጥ ሊያስገኙ በሚችሉ መስኮች ላይ ትኩት በመስጠት እንዲሰራ የማድረግና አልፎ አልፎም የግል ሴክተሩ የማይደፍራቸው ወይም የግሉ ሴክተር ደፍሮ ቢገባም በሚታሰበው ፍጥነትና አቅጣጫ ለውጥ አያመጣም ተብሎ በታመነባቸው መስኮች ላይ መንግስት ራሱ የሚሰራበት አካሄድ ይኖራል ለማለት ነው:: ምክንያቱም በታዳጊ አገሮች የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት በተለይ ደግሞ ቀጣይነት ያለው እድገት ለማስመዝገብ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ግንኙነቶችን የሚፈጥርና የሚቆጣጠር ጠንካራ መንግስት ይኖር ዘንድ የግድ ይላልና ነው::

በሌላ መልኩ ልማታዊ መንግስት ጣልቃ ይገባል ሲባል በዘፈቀደ ጣልቃ መግባት ማለት ሳይሆን ዓላማዎቹን ለማስፈጸም እና ከኢንቨስትመንትና ንግድ ጋር ትስስር ያላቸውን የተለያዩ አፈጻጸሞች (ለምሳሌ ቀረጥ፤ ብድር፤ ድጎማ፤ የገቢ ዕቃ ቁጥጥር፤ የወጪ ኤክስፖርት ፕሮሞሽን ወዘተ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን) ተገቢና ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ተግባር ላይ ያውላል ለማለት ነው::

ስለ ልማታዊ መንግስት ጣልቃ ገብነት ሌላው ግልጽ መደረግ የሚገባው ጉዳይ የጣልቃ ገብነቱ ስፋትና ይዘት በጊዜ እና የኢኮኖሚው እድገት ሲቀየር አብሮ የሚቀየር መሆኑ ነው:: የልማታዊ መንግስት ጣልቃ ገብነት በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች እንዲሁም ጣልቃ የተገባበት ጉዳይ የቆይታ ጊዜ (Life Span) የሚወሰን ይሆናል:: ይሁንና ብዙ ጊዜ የተለመደው በተለይ በዚህ ጉዳይ ላይ አመርቂ ውጤት አስመዝግበዋል ተብለው የሚጠቀሱት የጃፓንና የደቡብ ኮርያል ልምድ እንደሚያሳየው የልማታዊ መንግስት ጣልቃ ገብነት ምርቶችም ሆነ ኢንዱስትሪዎች ራሳቸውን ችለው እስከሚቆሙ (የተወዳዳሪነት ደረጃ እስከሚደርሱ ድረስ) ባሉት የመጀመርያ ጊዜያት እና ምርታማነታቸው የቀነሱና መወገድ የሚገባቸው ኢንዱስትሪዎች ለማስወገድ (በመጨረሻው ደረጃ) ላይ ይሆናል::

**2. ከግሉ ሴክተር ተጽእኖ ነጻ የመሆን (Autonomy)**

ልማታዊ መንግስት አስቀድሞ ባካበተው ሃብት አማካኝነት ወይም ሌሎች ባለሃብቶች ጥቅማቸውን እንዲያስጠብቅላቸው ወደ ስልጣን የሚያወጡት ሃይል አይደለም:: ልማታዊ መንግስት ያለማንም ተጽእኖ በተለይ ደግሞ ከግሉ ሴክተር ጫና ነጻ በሆነ መንገድ አገርን የማስተዳደር ሃላፊነት የወሰደ መንግስት ነው:: ልማታዊ መንግስት ከማንም ተጽእኖ ነጻ ነው ሲባል ግን ተባባሪ ወይም ተጣማሪ አካላት የሉትም ማለት አይደለም:: ከግሉ ሴክተር ጋርም በጠላትነት ወይም በጎሪጥ ይተያያል ማለትም አይደለም:: ልማታዊ መንግስት እንደ ሁኔታው

ከግሉ ሴክተር ጋር ተባብሮ መስራት ግዴታ የሚኖርበት ሲሆን ከአርሶ አደሩ ጋር ደግሞ ጥምረት ሊፈጥር ይችላል፡፡

የልማታዊ መንግስት ከግሉ ሴክተር ተጽእኖ ነጻ መሆን በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡ ከነዚህ ጠቀሜታዎች መካከል ከተጽእኖ ነጻ የሆነ መንግስት አገሪቱን ለመምራት በሚፈልግበት አቅጣጫ ያለምንም ጫና ሊያከናውን የሚችል ሲሆን ልማታዊ ባለሃብትን የሚያበረታታበት፤ በአንጻሩ ደግሞ በኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ የተጠመዱትን ደግሞ የማዳከምና የመቅጣት አቅጣጫ ለመከተል በእጅጉ ይረዳዋል፡፡ ከግሉ ሴክተር ተጽእኖ ያልተላቀቀ መንግስት እነዚህን ነገሮች በድፍረትና በነጻነት ሊያከናውን አይችልምና፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ልማታዊ መንግስት ወደ ስልጣን ሲመጣ ያለማንም ተጽእኖ በመሆኑ ከተባባሪዎቹ እና ከተጣማሪዎቹ ጋር በነጻነት ለመደራደር፤ ለመመካከር፤ የጋራ ይሁንታን ለመፍጠር፤ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ሪፎርሞች እና ማስተካከያዎች ላይ ከአጋሮች ጋር የትብብር መድረክ ለመፍጠር ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል፡፡ከዚህ አኳያ የልማታዊ መንግስት ከተጽእኖ ነጻ መሆን ሊደርስበት ወዳሰበው ግብ ለመድረስ የሚረዱትን ተባባሪዎች ለማፍራትና አቅጣጫ ለማስያዝ በእጅጉ ይጠቅመዋል ማለት ነው፡፡

ልማታዊ መንግስት ከተጽእኖ ነጻ መሆኑ መልካም ሆኖ ነገር ግን ይህ መንግስት ቀጣይነት ያለው ልማት እና እድገት ሊያስመዘግብ የሚችለው ከያገባኛል ባዮች ጋር ተጨባጭ የሆነ ግንኙነት መፍጠር ሲችል እንደሆነ በመስኩ ምርምር ያደረጉ ባለሙያዎች ይመክራሉ፡፡ ከነዚህ ያገባናል ባዮች ጋር የሚደረግ ግንኙነትም ከፖለቲካ ተጽእኖ ነጻ በሆነና በመተማመን ላይ ተመስርቶ ካልተሄደበት በስተቀር ውጤቱ አሉታዊ ሊሆን እንደሚችልም ይገልጻሉ፡፡ (ኢህአዴግ የአገራችንን ምርት ለማሳደግ አርሶ አደሩን በኤክስቴንሽን መርሐ-ግብር በማስገባት አርሶ አደሩን ከዚህ በፊት አይቶት ወደማያውቀው ሩጫ ሲያስገባው ምንም እንኳን ምርት በመጨመር ረገድ ውጤቱ አበረታች ቢሆንም አርሶ አደሩ« ይህ ስርዓት ሥራ አበዛብን፤ አደከመን» የሚል አቤቱታ እንዳቀረበው አይነት መሆኑ ነው፡፡ *በረከት ስምዖን የሁለት ምርጫዎች ወግ)*

በልማታዊ መንግስት ባህርያት ላይ ጥናት ያካሄዱ ተመራማሪዎች የልማታዊ መንግስት ከተጽዕኖ ነጻ የመሆን ጉዳይ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የነጻነቱ አድማስ ገደብ የተበጀለት (Embedded) ሲሆን እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ የልማታዊ መንግስት አውቶኖሚ የተገደበ ሲሆን ጥቃቅን ከሚመስሉ ነገር ግን ሥርዓቱን ሊያናጉ ከሚችሉ የግላዊነት አስተሳሰቦች በመራቅ የሥርዓቱን ውስጣዊ ጥንካሬ ቀጣይነት ለማስጠበቅ እንዲሁም ከኢኮኖሚ አጋሮቹ ጋር ወጥነት ባለው የግንኙነት መስመር ለመገናኘት ያስችላል ይላሉ፡፡ በግንኙነት መሃል ችግሮች ቢከሰቱም እንኳ ግልጽና ወጥ በሆነ መልኩ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራልና ነው፡፡

ሌላው የተገደበ አውቶኖሚ ትልቁ ጠቀሜታ ልማታዊ መንግስት ጣልቃ ሲገባ በዙርያ ምላሽ ሳይሆን በተመረጡና ዕድገቱንና ልማቱን ወደተፈለገው ጫፍ ሊያደርሱ በሚችሉ ለምሳሌ በመሰረተ ልማት ግንባታ ላይ እንዲያተኩር ስለሚያግዝ የውጤታማ ልማታዊ መንግስት አይነተኛ መገለጫ ይሆናል ማለት ነው::

**3. ጠንካራ ፈጻሚ አካል ማደራጀት (Bureaucratic Apparatus)**

በዕቅድ የተያዙትን የልማት ግቦች ለማሳካት ጠንካራ የፈጻሚ አካል ማደራጀት ለልማታዊው መንግስት የማይታለፍ ጉዳይ ነው:: በዚህ ዙርያ ጃፓኖች ልማታዊ ተግባራቶቻቸውን ለመከታተል አቋቁመውት የነበረው ዓለም አቀፍ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር (MITI) መ/ቤት እንደዚሁም ደቡብ ኮርያ ለተመሳሳይ ዓላማ ያዘጋጁትን የኢኮኖሚ ፕላኒንግ ቦርድ የሚጠቀሱ ናቸው:: የጃፓኑ (MITI) የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች በሁለት እግራቸው መቆም እስከሚችሉ ድረስ ወደ ጃፓን የሚገቡ  የፍጆታ ዕቃዎችን በተለይ ደግሞ የአገር ውስጥ ምርቶችን ሊወዳደሩ የሚችሉትን ለማዳከም እና እንዳይገቡ ለማድረግ የማይፈነቅለው ድንጋይ አልነበረም:: በአንጻሩ ደግሞ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እና ማሽነሪዎችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የማይረግጠው አገር አልነበረም::

እነዚህ አካላት የልማታዊው መንግስት የልማት ሂደት በበላይነት እንዲቆጣጠሩ፣ እንዲከታተሉና እንዲደግፉ የሚቋቋሙ ሲሆኑ የልማት ግቦቹን ለማሳካት በአገሪቱ ውስጥ ምርጥ ችሎታ ባላቸው ባለሞያዎች እንዲመሩም ይደረጋል:: ባለሞያዎቹ (ተቋማቱ) ሦሥት ቁልፍ ተግባራትም ይኖርዋቸዋል:: የመጀመርያው ተግባር እንዲለሙ የሚፈለጉትን ኢንዱስትሪዎች መለየትና መምረጥ ሲሆን ቀጣዩ ተግባር ደግሞ የተመረጡትን ኢንዱስትሪዎች በአፋጣኝ ሊለሙ የሚችሉበት የተሻለውን አማራጭ መንገድ/ስትራቴጂ/ መምረጥና መቀየስ ይሆናል:: በመጨረሻም እነዚህ ኢንዱስትሪዎች  በገበያው ውስጥ ተወዳዳሪነታቸውን ጠብቀው እንዲዘልቁ የመከታተል፣ የመቆጣጠርና የመደገፍ ተግባር ይሆናል:: እነዚህ የሚቋቋሙ የቢሮክራሲ ተቋማትም ተግባራቶቻቸውን ያለምንም ጫና ማከናወን እንዲችሉ ሙሉ ነጻነት የሚኖራቸው ይሆናሉ:: ባጠቃላይ የልማቱና የእድገቱ አቅጣጫ አገሪቱን የሚመራው አካል የሚያስቀምጥ ሲሆን አፈጻጸሙ ደግሞ የተቋቋመው ቢሮክራሲ ድርሻ ይሆናል ማለት ነው:: «Politicians reign and that the Bureaucrats rule » እንዲሉ::

**4. የግሉ ሴክተር ንቁ ተሳትፎ (Active participation of the private sector)**

ልማታዊ መንግስት በልማቱ ሂደት ከሚያጋጥሙት ከባድና ፈታኝ ሁኔታዎች መካከል ከግሉ ሴክተር ጋር የሚኖረው ግንኙነት አንዱና ግንባር ቀደሙ ነው:: ይህ ፈታኝ ሁኔታ በሁሉም አዳጊ እና ልማታውያን መንግስታት ዘንድ ሊያጋጥም የሚችል ፈተናም ነው:: ጃፓንን እንደ ማጣቀሻ ብንወስድ ላለፉት ከ 50 አመታት በላይ ይሄው ችግር ስታስታምም የኖች አገር

ነች:: እንደሚፈለገው ውጤት ባያስገኝላትም በተለያዩ ጊዜያት Self control፣ State control እንደዚሁም Cooperation የሚሉ ስትራቴጂዎችን በመቅረጽ በልማታዊው መንግስት እና በግሉ ሴክተር መካከል የነበሩትን ችግሮች ለመቅረፍ ሞክራለች::

**በልማታዊው መንግስት እና በግሉ ሴክተር መካከል የሚኖረው ግጭት ብዙውን ጊዜ የሚመነጨው የግሉ ሴክተር የፖሊሲ እና የአሰራር ክፍተቶችን ምክንያት በማድረግ በክፍተቱ ለመጠቀምና በአቋራጭ ለመክበር ሲሯሯጥ፣ በአንጻሩ ልማታዊው መንግስት ደግሞ ይህንን አሰራርና አስተሳሰብ ለመከላከል እና ለማቀጨጭ በሚያደርገው ጥረት መካከል በሚፈጠሩ የጥቅም ግጭቶች ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ልማታዊው መንግስት አሳካዋለሁ ብሎ ለሚያስበው የኢንዱስትሪ ልማትና የኢኮኖሚ ዕድገት መነሻውና መሰረቱ ግብርናና አርሶ አደር ነው ብሎ ስለሚያምን በከተሞች ያለውን የግል ሴክተር የሂደቱን ዋና ተዋናይ አድርጎ ያለመውሰድ አዝማሚያዎች ናቸው::** ይሁንና ምንም እንኳ የልማታዊው መንግስት መሰረት ግብርናውና አርሶ አደሩ ቢሆኑም ባለሃብቱና የግሉ ሴክተር በልማቱ ሂደት ላይ ንቁ ተሳትፎ ካላደረገ በስተቀር ልማታዊው መንግስት የሚፈልገውን የኢኮኖሚ እድገት ለማሳካት አዳጋች እንደሚሆንበት ጥናቶች ያመላክታሉ::

*ስለ ልማታዊ መንግስት መለያ ባህርያት ይህን ካልን ከነዚህ መለያ ባህርያት አንጻር የኢትዮጵያ መንግስት ምን ደረጃ ላይ ይገኛል የሚለውን ከዚህ በታች ለመዳሰስ ተሞክሯል::*

የኢትዮጵያ መንግስት በኢትዮጵያ እንደ ሕዝብም እንደ አገርም የመጀመርያው ጠላት ድህነት በመሆኑ ይህ ዋና ጠላት ለማጥፋት በመጀመርያ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኃላ ቀር አገሮች ድህነትን በግማሽ ለመቀነስ በሚል የተያዘውን የሚለንየም እቅድ ለማሳካት፣ ከዚሁ በመቀጠልም አገራችን ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ አቆጣጠር እስከ 2017 ዓ.ም ድረስ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የሚል ሰፊ ራዕይና ግብ በማስቀመጥ፣ ለዚህም ተፈጻሚነት ይረዳ ዘንድ የልማታዊ መንግስት የልማት መስመሮች በመከተል ሰፋፊ የልማት ዕቅዶች በማቀድ ወደ ስራ መገባቱ ይታወቃል::

ከላይ የልማታዊ መንግስት መለያ ባህርያት ብለን ካስቀመጥናቸው ባህርያት መካከል የመንግስት ጣልቃ ገብነት አንዱና ዋነኛው ነው:: ልማታዊው መንግስት ጣልቃ የሚገባውም የእድገቱን ሂደትና አቅጣጫ ለመቆጣጠር፣ አሰሪ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎችን ቀርጾ ወደ ስራ በማስገባት እና የግሉ ሴክተር በማይደፍራቸው፣ ቢደፍራቸውም የታሰበውን ያህል ፍጥነትና በታሰበው አቅጣጫ ላይመራው ይችላል ተብሎ በታመነባቸው ሴክተሮች ልማታዊው መንግስት ራሱ በሚመራው ቢሮክራሲ እንደሚያከናውነው አይተናል::

ከዚህ አንጻር የአገራችንን ድህነት ሊያስወግዱ የሚችሉ እና ወደ ብልጽግና ጎዳና ሊመሩ የሚችሉ አጓጊ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ተቀርጸው እየተሰራባቸው ነው:: የአገራችን የኢኮኖሚ እና እድገት አቅጣጫዎች በመምራትም መንግስት ተገቢ ሚናውን እየተጫወተ ነው::

*የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ደፍሮ ሊገባባቸው ያልቻለ እንደ መሰረተ ልማትና የኃይል ማመንጨት የመሳሰሉ ዘርፎችም መንግስት በራሱ ቢሮክራሲ እየመራ አመርቂ የሚባል ውጤት እያሳየ ነው፡፡ የፋይናንስ ተቋማት ከውጭ ሃይል በመጠበቅ በመንግስትና በዜጎች እጅ ብቻ ተገድቦ እንዲቆይ መደረጉም የታሰበው ስራ ያለመሰናክል ለማስኬድ ዋና መሳርያ ስለሚሆን ተመራጭ ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ መንግስት ከቢራ ገበያ ሙሉ በሙሉ በመውጣት የቢራ ኢንዱስትሪው ወደ ግሉ ዘርፍ እንዲዛወር ማድረጉ የመንግስት ጣልቃ ገብነት የተገደበ እንደሆነ ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ መንግስት የልማታዊያን መንግስታት ፈለግ እየተከተለ መሆኑ በግልጽ ማየት ይቻላል፡፡* ***ይሁንና አልፎ አልፎ የሚታዩ የመንግስት ጣልቃ ገብነቶች ጥናት ላይ ያልተመሰረቱና የማያዛልቁ እንደ የችርቻሮ ዋጋ ተመኖች የመሳሰሉ እርምጃዎች መንግስት ከተባባሪዎቹ ( ደጋፊዎቹ) ጋር ወደ ግጭት የሚመራው ከመሆኑም ባሻገር በዋና ዋና ተግባራት ላይ ትኩረት እንዳያደርግ ከዋና መንግድ የሚያዘናብሉ በመሆናቸው እንደዚህ አይነት እርምጃ ሲወሰድ በመጀመርያ ጥናት ላይ እንዲመሰረት ብሎም ዘላቂነቱ እና ለሕዝብ ያለው ጠቀሜታ በጥልቀት እየታየ ከማስኬድ አንጻር አሁንም ረጅም ርቀት የሚቀር ይመስላል፡፡***

*ሌላው የልማታዊ መንግስት መለያ ባህርይ ከግሉ ዘርፍ ተጽእኖ ነጻ መሆንን ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ማሕበራዊ መሰረቱ አርሶ አደሩ እንደመሆኑ መጠን ተጽእኖ ካጋጠመው ከመሰረቱ ከአርሶ አደሩ እንጂ ከግሉ ዘርፍ ሊሆን እንደማይችል መገመት አያዳግትም፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት የኢትዮጵያን ሕዝብ ከድህነት አላቅቃለሁ ሲልም አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሸፍነው  አርሶ አደሩን በመያዝ እንጂ ጥቂቱን የግል ዘርፍ ተማምኖ እንዳልሆነም ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በመርህ ደረጃ የኢትዮጵያ መንግስት ወደ ስልጣን ሲመጣም በስልጣን ቆይታውም ከግሉ ዘርፍ ተጽእኖ ነጻ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይሁንና ግን በዚህ ረገድም መጥራት ያለበት ጉዳይ አለ፡፡* ***መንግስት እንደ መንግስት በተለይም የበላይ አመራሮቹ በዚህ ረገድ ጠንካራ አቋም እንዳላቸው የሚታመን ቢሆንም ወደ አፈጻጸም ሲወረድ ግን የታሰቡትን የልማት ግቦች ከግብ ከማድረስ አንጻር ሰፊ እንቅፋት ሊፈጥር የሚችል በመንግስት ተሿሚዎች እና አስፈጻሚዎች ላይ የግሉ ዘርፍ ተጽእኖ በሰፊው ይስተዋላል፡፡***

*ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የመንግስት ከግሉ ዘርፍ ተጽእኖ ነጻ መሆን በተለይ ልማታዊውን ባለሃብት ለማበረታታትና ለመሸለም፤ በአንጻሩ ደግሞ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጨማሪ እሴት የሌላቸውን የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰቦችና አሰራሮች የተጠናወታቸውን ለማቀጨጭ ብሎም ለማጥፋት በነጻነት እንዲሰራ ስለሚያስችለው ነው፡፡ በተጨማሪም መንግስት ራሱን ችሎ ከተባባሪዎቹ ጋር ለመደራደር አስፈላጊ ሲሆንም በራሱ ጊዜ የልማት ዕቅዶቹን ለማስፈጸም ስለሚያስችለው ነው መንግስት ከግሉ ዘርፍ ተጽእኖ ነጻ መሆን አለበት የሚባለው፡፡* ***ይሁንና የኢትዮጵያ መንግስት በዚህ ረገድ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመድፈን የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እያደረገ ቢሆንም የግሉ ዘርፍ በመንግስት ቢሮክራሲ ስር የተዋቀሩትን መ/ቤቶች በእጅ አዙር የመምራት፤ የልማታዊው መንግስት ውሳኔዎች እና ስትራቴጂዎች ወደ ጎን***

**በመተው ወይም በመሸርሸር ለግል ጥቅም በሚያመች መልኩ እንዲተገበሩ የማድረግ አዝማሚያዎች በስፋት ስለሚታዩ፣ ጊዜ ሳይወስዱ ካልተስተካከሉ የልማታዊው መንግስት ግቦች ሊያኮላሹ ስለሚችሉ ችግሮቹን ለማስወገድ መረባረብ የሚገባ ይሆናል፡፡**

ጠንካራ ፈጻሚ አካል ማዘጋጀት ሌላው የልማታዊ መንግስት መለያ ባህርይ ነው፡፡ ከላይ ለማስቀመጥ እንደተሞከረው ልማታዊው መንግስት ለነደፋቸው የልማት ግቦች መሳካት የሚያደራጃቸው የቢሮክራሲ አካላት አገሪቱ ውስጥ አሉ በሚባሉ ባለሙያዎች መመራት ይገባቸዋል፡፡ ስራዎቻቸውን በተሳካ መልኩ እንዲያከናውኑም በነጻነት መስራት እንደሚገባቸው ተገልጿል፡፡ ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ መንግስት እንደ ጃፓንና ኮርያ የልማት ስራዎችን የሚከታተል ራሱን የቻለ አካል ከማቋቋም ይልቅ የልማት ስራዎቹ በሴክተር መ/ቤቶች ስር እንዲከናወኑ አድርጓል፡፡ የግብርናው ልማት በግብርና ሚኒስቴር፣ የኃይል ልማት  በኢነርጂ ሚኒስቴር፣ የኢንዱስትሪው በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወዘተ፡፡ የልማት ስራዎቹን የሚከታተል አንድ አካል ማቋቋም ወይም ልክ እንደ ኢትዮጵያ በየዘርፉ በማከፋፈል እንዲተገበሩ ማድረግ ላይ የአካሄድ ጉዳይ ስለሆነ ብዙም የሚያከራክር ጉዳይ አይሆንም፡፡ ሊያከራክርና ሊያነጋገር የሚችለው እነዚህ የልማት ግቦች ለማሳካት የተቋቋሙ አካላት የሚመሩት እና በውስጣቸው የሚሰሩት ባለሙያዎች አገሪቱ ውስጥ በመስኩ አሉ የሚባሉት ናቸው ወይስ እንደማንኛውም መ/ቤት ለስራ ያመለከተ የተሰበሰበባቸው ናቸው የሚለውን ነው፡፡ ከሁለት ዓመታት በፊት «ንግድና ኢንዱስትሪ» ይባል የነበረው ሚኒስቴር መ/ቤት ለሁለት ተከፍሎ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ራሱን የቻለ እንዲሆን ተደርጎ መዋቀሩ አቅጣጫ ጠቋሚ በመሆኑ አንድ አዎንታዊ እርምጃ ነው፡፡ ነገር ግን በብዙ ሚኒስቴር መ/ቤቶች እንደሚታየው ***«አመራሮቹም ሆኑ ሰራተኞቹ በጊዜ የለንም»*** ስሜት ሳይሆን በተለምዷዊው አሰራር ሲጓዙ ማየት የተለመደ ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህን ተቋማት እንዲመሩ እና በውስጣቸው እንዲሰሩ የሚደረጉት ዜጎችም በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኙ ምርጥ ችሎታ ካላቸው መካከል የተሻሉት መሆናቸውን በእርግጠኝነት መናገር አዳጋች ነው፡፡

የግሉ ሴክተር (የንግዱ ማህበረሰብ) በልማታዊ ስራዎች በንቃት እንዲሳተፍ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና ማነሳሳት ሌላው የልማታዊ መንግስተ የቤት ስራ ነው፡፡ የልማታዊ መንግስት ምንነት ስንገልጽ ልማታዊ መንግስት ኒዮ-ሊበራልም ያልሆነ፣ ሶሻሊስትም ያልሆነ ሥርዓት እንደሆነ፣ የሁለቱንም አዎንታዊ ገጽታዎችን በማጣመር የሚተገበር መሆኑን ገልጸናል፡፡ ስለሆነም ልማታዊው መንግስት የእድገት ግቦቹን ለማሳካት የግሉን ሴክተር ማሳተፍ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ ለነገሩ የልማታዊ መንግስት ጣልቃ ገብነት ስናወራም ጣልቃ ገብነቱ ዙርያ ምላሽ ሳይሆን በተመረጠ አኳሃን መሆን እንደሚገባም አይተናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የልማታዊው መንግስት ዓላማ የሚመራውን አገር ከድህነት ማላቀቅ እና ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ መፍጠርን ስለሆነ ይህንን ግብ ካሳካ በኃላ ኢኮኖሚውን የመምራት ሚና ባብዛኛው ወደ ግሉ

ዘርፍ የሚዛወር በመሆኑ የግሉ ዘርፍ እና ልማታዊው መንግስት ተባብረው መስራት የግድ ይላቸዋል፡፡

የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ ተግባራዊ አድርገው በበለጸጉት አገሮች እንዲሁም በአገራችንም በሰፊው እንደሚስተዋለው የግሉ ሴክተር ሕጎችና አሰራሮችን ከተቻለ ባለመከተል ግፋ ቢልም በመሸራረፍ ከሕግ ውጭ በመሆን ለመጠቀም በመፈለግ፤ መንግስት ደግሞ ይህንን ስርዓት አልበኝነት ለማጥፋት በሚደረግ ፍትጊያ በነዚህ ሁለት አካላት መካከል ሁሌም ግጭት መፈጠሩ አይቀርም፡፡ ግጭት መፈጠሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ግጭቱን ለመፍታት የሚወሰዱት እርምጃዎች ግን ኢኮኖሚውን ለማሳደግ እና የልማት ግቦቹን በስኬት ለመፈጸም ወሳኝ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

ከዚህ አንጻር ከአገልግሎትና መልካም አስተዳደር ጋር የተያያዙ መሰናክሎች እንደተጠበቁ ሆነው የኢትዮጵያ መንግስት የግሉን ዘርፍ ሊያሰራ የሚችል ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል ብለን መውሰድ እንችላለን፡፡ ከግሉ ዘርፍ ጋር የሚፈጠሩትን ግጭቶች አፈታት ላይ ግን ረጅም መንገድ የሚቀር መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ በጣም ጥቂት ባለሃብቶች መልካም ስነምግባርን የተከተለ (Ethical) ቢዝነስ የሚያካሂዱ ቢሆኑም አብዛኛው ባለሃብትና ነጋዴ ነግዶና ሰርቶ የሚኖርባት አገር የተረጋጋች፤ ንግዱና ስራውም ቀጣይነት ሊኖረው የሚችለው የሚገባውን ሲፈጽም እንደሆነ አለማወቅ ወይም ለማወቅ አለመፈለግ፤አገሪቱን የሚመራ መንግስት ሰላምና ጸጥታን በማስፈን ሰርቶና ነግዶ ለመኖር አስተማማኝና ምቹ ሁኔታ ይፈጥርልኛል ከማለት ይልቅ መንግስትን እንደ ጠላትና ቀማኛ አድርጎ መፈረጅ ፤ተጠቃሚውን እንደ ሸሪክና የህልውናው ምክንያት እንደሆነ አድርጎ ከመቁጠር ይልቅ ጭራሽ የጠላት ያህል መሰረት የሌለው የዋጋ ጭማሪ ማድረግን፤ምርቶች መደበቅን፤ በምርቶች ላይ ባእድ ነገሮች በመጨመር ማቅረብ፤ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምርቶች መሸጥ ወዘተ በአገራችን የተለመደ ነው፡፡

**በመንግስት በኩልም ጠንካራና ለግሉ ዘርፍ ተጽእኖ የማይንበረከክ፤ የግሉ ዘርፍ ላይ ተጽእኖ በማሳደር በልማታዊው መንግስት የተነደፉ የልማት ግቦች ለማሳካት የሚችል፤ የግሉን ዘርፍ በአግባቡ ሊያንቀሳቅስ የሚችል መዋቅር በአግባቡ አለመዘርጋት፤ጥናት ላይ ያልተመሰረቱ እና በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚፈርሱ ሕጎች ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ በዚህም የተነሳ በአግባቡ የሚነግደውን ነጋዴ በመንግስት ሕጎች ላይ እምነት እንዲያጣ፤ጠንካራ ሕግ እንዲኖር የማይፈልገው ደግሞ መንግስትን ለማጥላላት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥርለት ማድረግ፤ ወዘተ በተደጋጋሚ የሚስተዋሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡** ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዋና ዋና ከሚባሉት ነጋዴዎች ጋር ሲወያዩ ከነጋዴዎቹ መካከል ***«የምታወጡት ሕግ ባይሰራስ፤ውጤታማ ባይሆንስ ምን ታደርጋላችሁ»*** የሚል ጥያቄ መቅረቡ በመንግስት የሚወጡትን ሕጎች በነጋዴው ዘንድ እምነት እና ጥንካሬ የታጣባቸው መሆናቸው መገንዘብ የሚያስችል አጋጣሚ ነው፡፡ መንግስትና

የግሉ ማህበረሰብ እንዲህ በጎሪጥ እየተያዩ የተያዙትን ሰፋፊ የልማት ግቦች በስኬት ማከናወን አዳጋች እንደሚሆንም መገመት አያዳግትም፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) አባል ለመሆን የመጀመርያውን ዙር ድርድር አልፋ ወደ ቀጣዩ ዙር ተሻግራለች፡፡ የዚህን ድርጅት አባል መሆን እንደ አገር የሚያሥገኘው ጥቅም እንደተጠበቀ ሆኖ አባል ከተሆነ በኃላ የሂቱ ዋና ተዋናይ የሚሆነው መንግስት ሳይሆን የንግዱ ማህበረሰብ እንደሆነም ይታወቃል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለን ነጋዴ (በጣት ከሚቆጠሩት ውጪ) የገበያን ሕግ መሰረት በማድረግ እንደየሁኔታው የሚተጣጠፍ ሳይሆን በልማድ የተተበተበ ስለሆነ በአገር ውስጥ ገበያ የተስተካከለ ባህርይ ሳይኖረው በአለም አቀፉ ገበያ ገብቶ ውጤታማ ይሆናል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው የሚሆነው፡፡ በመሆኑም በመንግስትና በንግዱ ማህበረሰብ መካከል የሚታየውን በጎሪጥ የመታየት ችግር ለመቅረፍ እንደ ጃፓን ሶስት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሶስት ጊዜ ሶስት የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በመቀየስ ሁለቱንም አካላት ተደጋግፈው የሚሰሩበት መንገድ ቢፈለግ መልካም ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ የሚመጣው ልማት ድህነትን ለማስወገድ እና የጋራችን የሆነችው ኢትጵያውያን ለማበልጸግ በመሆኑ የጋራ መፍትሔ የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው የኢትዮጵያ መንግስት የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ አንግበው የበለጸጉ አገሮችን ፈለግ ተከትሎ አገራችንን በእድገት ጎዳና እየመራት ነው፡፡ ይሁንና በእድገቱ መሰናክል ሊሆኑ የሚችሉ በተለይ ጠንካራ አስፈጻሚ አካልን የማደራጀት እና ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር ያለውን ጤነኛ ያልሆነ ግንኙነት በአፋጣኝ ማሻሻል ለነገ የማይባሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የልማታዊ መንግስት መርሆዎች መከተል ልማትን ለማረጋገጥ ተመራጭ መንገድ ቢሆንም የልማታዊ መንግስት መርህ መከተል በራሱ ጊዜ ልማትን እንደማያመጣ መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የልማታዊ መንግስት መርህ ከአደጋ የጸዳ አለመሆኑም መገንዘብ መልካም ይሆናል፡፡ የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ ይከተሉ የነበሩ የላቲን አሜሪካ አገሮች  እ.ኤ.አ በ **1980ዎቹ** የተከሰተባቸው የዕዳ ቀውስ፤ እ.ኤ.አ በ **1990ዎቹ** በጃፓን ያጋጠመው የእድገት ማሽቆልቆል፤በተመሳሳይ መልኩ እ.ኤ.አ በ **1997** በምስራቅ ኤዢያ ያጋጠመው የገንዘብ ቀውስ  ልማታቸውን በማደናቀፍ ወደ መቆም ደረጃ በመድረሳቸው ምክንያት በልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ ውጤታማነት ላይ ትልቅ ጥያቄ ተነስቶ የነበረ በመሆኑ «ትምህርትን አታሳጣኝ፤ ማስተማርያም አታድርገኝ» እንዲሉ ከኛ በፊት መስመሩን ይከተሉ በነበሩ አገሮች ላይ ደርሶ የነበረውን ቀውስ እንዳይመታን ከወዲሁ መዘጋጀቱ ብልህነት ነው፡፡

ለአስተያየትዎ፡- jhoniabraha@gmail.com